የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Authority for Civil Society Organization

ስለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ክትትል፣ ቁጥጥር እና ምርመራ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1002/2016	**Directive on monitoring, control, and investigation of civil society organization No. 1002/2024**
በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) ከአዋጁ ዓላዎች አንዱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በተመዘገቡበት ዓላማ መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን በመከታተልና በመቆጣጠር የሕብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሆነ የተደነገገ በመሆኑ፤	Where as, As it is stated in sub-article (2) of article 5 of the proclamation one of the provisions of the proclamation is to ensure the greater benefit of the society by monitoring and controlling the performance of civil society organizations according to the purpose for which they are registered;
በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 አንቀጽ 6 ንዑስአንቀጽ (2) መሠረት ባለስልጣኑ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሥራቸውን በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን እና ተግባር የተሰጠው በመሆኑ፤	Where as, the Authority has the powers and functions vested in it by Article 6(10) of the Proclamation to monitor and control the civil society organizations to ensure that they carry out their work in accordance with the law;
በአዋጁ አንቀጽ 77 ንዑስአንቀጽ (1) ከመንግሥት አካላት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከሕዝብ ከሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ባለስልጣኑ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከሚገኙ መረጃዎች በመነሳት ማናቸውም ድርጅት ሥራውን በሕግ መሠረት እየሰራ ስለመሆኑ ባለስልጣኑ ምርመራ ማድረግ እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ፤	Where as, it is stated in sub-article (1)of article 77 of the proclamation granted the authority to investigate whether any organization is doing its work according to the law, based on suggestions from government bodies, donor organizations or the public, or based on information obtained while the authority is performing its work;
ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡	Therefore, it is necessary to issue directive to implement the above-mentioned provisions, the authority of civil society organizations has issued this guideline according to the authority given by Article 89 sub-paragraph (2) of the decree.

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Authority for Civil Society Organization

ክፍል አንድ **ጠቅላላ**	**Section One** **General**
1. አጭር ርዕስ ይህ መመሪያ "ስለክትትል፣ ቁጥጥርና ምርመራ መመሪያ ቁጥር 1002/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡	**1. Short Title** This Directive may be cited as the "Monitoring, Control and Inspection Directive No. **1002/2024**.
2. ትርጓሜ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ፤	**2. Definitions** Unless the context requires otherwise, in this Directive:
1) "ክትትልና ቁጥጥር" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ድርጅቶች በተዘገቡበት አላማ እና በህግ መሰረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን በባለስልጣኑ በዴስክ፣ በመስክ፣ ጥቆማን መሰረት በማድረግ እና ባለስልጣኑ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከሚገኙ መረጃዎች በመነሳት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡	1. "Monitoring and control" means that according to Article 5, Sub-article 2 and Article 6, Sub-Article 2 of the proclamation, organizations are carrying out their work according to the purpose and in accordance with the law.
2) "ምርመራ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከመንግሥት አካላት፣ ከስጋሽ ድርጅቶች ወይም ከሕዝብ ከሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ባለስልጣኑ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከሚገኙ መረጃዎች በመነሳት ማናቸውም ድርጅት ሥራውን በሕግ መሠረት እየሰራ ስለመሆኑ የሚያካሂደው የማጣራት ተግባር ነው፡፡	2. "Investigation" means, according to Article 77 Sub-Article 1 of the proclamation, the act of investigating whether any organization is doing its work in accordance with the law, based on suggestions from government bodies, donor organizations or the public, or based on information obtained while the official is performing his work
3) "የመስክ ክትትልና ቁጥጥር" ማለት በድርጅት ወይም ፕሮጀክት በመገኘት የድርጅቱን የስራ አመራርና ሌሎች ሰራተኞችን እንዲሁም ጉዳዩ በሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚገኙ የአመራር አባላትና ሰራተኞች እንዲሁም የድርጅቱ አባላትና ተጠቃሚዎች ሶስተኛ ወገኖችን በማነጋገር፣ ቃለ ምልልስ	3. Field monitoring and control means the management and other employees of the organization or project, as well as the relevant government offices; Contacting third parties of management members and staff of non-governmental organizations as

በማድረግ እና መረጃ በመሙሰድ የሚከናወን ክትትልና ቁጥጥር ነው፡፡	well as members and beneficiaries of the organization; Monitoring and control is done by interviewing and taking information.
4) መርማሪ“ ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጸውን ምርመራ ለማካሄድ በባለስልጣኑ የሚመደብ የባለስልጣኑ ወይም ከባለስልጣኑ ውጭ ያለ ባለሙያ ማለት ነው፤	4. "Investigator" means an expert of the authority or outside the authority assigned by the authority to carry out the investigation described in sub-article 2 of this article;
5) አዋጅ“ ማለት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ነው፤	5. "Proclamation" means Proclamation No. 1113/2011 of Civil Society Organizations;
6) በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤	6. “Interpretations given in the proclamation shall also apply to this directive;
7) በወንድ ፃታ የተገለጸው አነጋገር የሴት ፃታንም ይጨምራል፡፡	7. The male gender includes the female gender.
3. የተፈጻሚነት ወሰን ይህ መመሪያ በማንኛውም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡	**3. Scope of Application** This directive applies to any civil society organization
4. ዓላማ	**4. Purpose**
የዚህ መመሪያ ዓላማ፤	Purpose of this directive;
1. ድርጅቶች ሥራቸውን በሕግ እና በተቋቋሙበት አላማ መሠረት ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ አንዳስፈላጊነቱ ምርመራ በማድረግ ድርጅቶች ለህተታቸውን በማረም ለበለጠ ስኬት እንዲበቁ እና ውጤታማና ዘላቂነት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ማገዝ፤	1. To ensure that organizations carry out their work in accordance with the law and the purpose of their establishment, by conducting investigations as necessary, helping organizations to correct their

	mistakes and achieve greater success and to provide effective and sustainable services;
2. የድርጅቶቹ አሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት ያስበት እንዲሆን በማስቻል የህብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤	2. Ensuring the greater benefit of the society by enabling the organizations to be transparent and accountable;
3. በማንኛውም ድርጅት ውስጥ ሕገወጥና ከተቋቋመበት ዓላማ ያፈነገጠ ድርጊት ተፈጽሞ ሲገኝ ምርመራ በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤ እና	3. In any organization, when it is found that an act that deviates from the purpose of its establishment has been committed, conduct an investigation and take corrective action; And
4. በድርጅቶች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር፣ ክትትል እና ምርመራ ወጥነት ያለውና ተገማች እንዲሆን በማድረግ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን የተላበሰ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጉ ማስቻል ነው፡፡	4. Controlling, monitoring and investigation on organizations is to make it consistent and predictable, enabling them to develop a transparent and accountable operating system.
ክፍል ሁለት **ስለቁጥጥር እና ክትትል**	**Section Two** **control and monitoring**
5. መርሆዎች	**5. Principles**
1. ባለስልጣኑ የክትትልና ቁጥጥር የሚያደርገው በቢሮ ውስጥ በዴስክ ክትትልና ቁጥጥር ማለትም በባለስልጣኑ እጅ ከሚገኙ ዓመታዊ የሥራ እንቅስቀሴ፣ የኦዲት ሪፖርት እና የፕሮጀክት ሰነዶችና ስምምነቶች፤ ከድርጅቱ፣ ከመንግሥት፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከሦስተኛ ወገኖች በተለያዩ መንገዶች የሚገኙ ሰነዶችና መረጃዎች መሠረት በማድረግ ይከናወናል፡፡ ሆኖም ባለስልጣኑ በቂ ምክንያት ካለው የሚከተሉትን መርሆች መሰረት በማድረግ የመስክ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይችላል፤	1. The Autority conducts monitoring and control in the office through desk monitoring and control, that is, from the annual work motion, audit report and project documents and agreements in the hands of the official; it is done on the basis of documents and information available in various ways from the organization, government, non-governmental organizations and third parties. However, if the authority has sufficient reason, it can conduct field

	monitoring and control based on the following principles;
ሀ) ባለስልጣኑ በድርጅቶች ላይ የሚያካሂዳቸው የቁጥጥርና የክትትል ሥራዎች ወጥነት ያለውና የቁጥጥሩ ወይም የክትትሉ አፈጻጸም ወሰን ተፈጽሟል የተባለውን ወይም ሊፈጸም ይችላል ተብሎ በቂ ምክንያት ሊቀርብበት የሚችለውን ድርጊት ለማጣራት በሚያስፈልገው መጠን ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡	a) The control and monitoring activities carried out by the authority on organizations should be consistent and the scope of the control or monitoring performance should be only to the extent necessary to check the actions that are said to have been done or that may be done.
ለ) ማናቸውም ክትትልና ቁጥጥር የሚከናወነው የሚመለከታቸውን የአመራር አባላትና ሌሎች ሠራተኞችን በማዳመጥና ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልጹ በማድረግ ነው፡፡	b) Any monitoring and control is done by listening to the relevant management members and other employees and allowing them to express their opinions freely.
ሐ) በባለስልጣኑ የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር ድጋፋዊ ሆኖ ቁጥጥር ወይም ክትትል በሚደረግበት ድርጅት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽህኖ የማይፈጥር መሆን ይኖርበታል፡፡	c) Monitoring and control by the authority should be supportive and not create a negative impact on the day-to-day activities of the organization being monitored or monitored.
2. ከላይ የተጠቀሱት መርሆች ባለስልጣኑ ለሚያደርገው የመስክ ክትትልና ቁጥጥር ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡	2) The principles mentioned above are applicable to the field monitoring and control carried out by the authority.
6. ክትትልና ቁጥጥር ስለሚደረግበት ሁኔታ	**6. Monitoring and supervision**
1) ባለስልጣኑ ድርጅቶች ሥራቸውን በህግ እና በተቋቋሙበት አላማ መሠረት ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ በዋናነት በጥቆማዎች ላይ በመመስረት ወይም ባለስልጣኑ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከሚገኙ መረጃዎች በመነሳት አጠቃላይ ወይም የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ በመስክ ወይም በዴስክ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይችላል፡፡	1) In order to ensure that organizations carry out their work in accordance with the law and the purpose for which they were established, the authority shall conduct field or desk monitoring and control on general or specific issues based on suggestions or based on information available during the authority's work.

2) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተገለፁት ሁኔታዎች መሠረት ለሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር ዓመታዊ የቁጥጥርና የክትትል ዕቅድ ያወጣል፡፡	2) The authority shall draw up an annual control and monitoring plan for monitoring and control according to the conditions described in sub article (1) of this article.
7. ክትትልና ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች	**7. About matters to be monitored and controlled**
1. ባለስልጣኑ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል፤	1. The authority shall monitor and control the following issues;
(ሀ) አንድ ድርጅት የሚያንቀሳቅሰውን ገንዘብና የሥራውን ስፋት የሚመጥን የውስጥ የቁጥጥር እና የፋይናንስ እና ግዢ ሥርዓት የሌለው መሆኑን የሚያሳይ መረጃዎች ሲኖረው፤	(a) When there is evidence that an organization does not have an internal control and financial and purchasing system that is adequate to the funds it operates and the scope of its operations;
(ለ) የድርጅቱ የሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ ወይም አሰራር ላይ ችግሮች እንዳሉ መረጃ ሲኖረው፤	(b) when he has information that there are problems with the organization's personnel management guidelines or procedures;
(ሐ) ድርጅቱ የህግ አለመከበር ሲያጋጥመው የሚለይበትና መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል ስርአትና አሰራር እንደሌለው የሚጠቁም መረጃ ሲኖረው፤	(c) When the organization has information indicating that it does not have a system and procedure to identify and resolve when it encounters a violation of the law;
(መ) ድርጅቱ የሚያገኘው ገንዘብ ህገ ወጥ ከሆነ ምንጭ የተገኘ ለመሆኑ የሚያጠራጥሩ ሁኔታዎች ሲኖሩ እንዲሁም ከተሰገሰው ገንዘብ ጋር የተያያዙ ቅድመ ሁኔታዎች ህግን የሚጻረሩ ሆነው ሲገኙ፤	(d) When there are suspicious circumstances that the money received by the organization is obtained from an illegal source, and when the conditions related to the donated money are found to be against the law;
(ሠ) ተጠቃሚዎች ያሉት ድርጅት ተጠቃሚዎቹን ለመምረጥ የሚጠቀምበት መመዘኛና ስርአት ግልጸኝነትና ተአማኒነት የሌለው ስለመሆኑ መረጃ ሲኖረው፤	(e) When the organization with users has information about the lack of transparency and credibility of the criteria and system used to select the users;

(ረ) ከጋሾች የሚሰጥ ገንዘብ ህግንና የታክስ ሥርዓቱን የተከተለ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ አሰራር ያለ መሆኑ ሲደረስበት፤	(f) When it is found that there is a procedure to ensure that money given by donors does not follow the law and the tax system;
3) እያንዳንዱ ድርጅት ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተዘረዘሩት ሳይ ለሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር አስፈላጊውን ሰነዶች በማቅረብና ለሚቀርብለት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽና ማብራሪያ በመስጠት መተባበር ይኖርበታል፡፡	3) Every organization should cooperate by providing the necessary documents for the monitoring and control of the authorities listed in sub- article (1) of this article and by giving appropriate responses and explanations to the questions presented to them.
ክፍል ሦስት **ሰለምርመራ**	**Section Three** **Investigation**
8. በድርጅቶች ላይ የሚካሄድ ምርመራ ዓላማ	**8. The purpose of investigation on organizations**
በድርጅቶች ላይ የሚካሄድ ምርመራ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡	An investigation into organizations will have the following objectives.
1) ድርጅቶች ህግን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ የማድረግ 2) በተመረጡ ጉዳዮች ዙሪያ በድርጅቶች ደረጃ ሊታይ የሚችልን ህግ ለማክበር ወይም ህገወጥ አካሄድን ለይቶ ለማውጣት እና ተገቢውን የእርምት እርምጃ የመውሰድ፤	1) To make organizations comply with the law 2) To identify non-compliance with the law or illegal behavior that can be observed at the level of organizations around selected issues and take appropriate corrective action;
3) በምርመራ ሂደት የሚገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የድርጅቶችን የራስ አስተዳደር የማበረታታት፤	3) Encouraging the self-management of organizations based on the information found in the investigation process;
9. ምርመራ ስለማድረግ	**9. conducting an investigation**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Authority for Civil Society Organization

1) በአዋጁ አንቀጽ 77 በተደነገገው መሠረት ባስልጣኑ በቂ ምክንያት ካገኘ ከመንግሥት አካላት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከሕዝብ ከሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ለባለስልጣኑ ከደረሱ መረጃዎች ወይም ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት ክትትል እና ቁጥጥር በሚያከናውንበት ጊዜ ከሚገኝ መረጃ በመነሳት በአንድ ድርጅት ላይ አጠቃላይ ወይም የተወሰነ ግብ ያለው ምርመራ ማካሄድ ይችላል፡፡	1) According to Article 77 of the proclamation, if the authority finds sufficient reason, based on suggestions from government bodies, donor organizations or the public, or information received by the authority, or information obtained when the authority carries out monitoring and control in accordance with Article 6 of this directive, it may conduct a general or specific investigation on an organization. .
2) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ምርመራ ለማድረግ በቂ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ ምርመራ የሚያከናውን እንደ ጉዳዩ ክብደት አንድ መርማሪ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ መርማሪዎች ከባለስልጣኑ ሠራተኞች መካከል ወይም የተለየ ክህሎት የሚጠይቅ የሆነ እንደሆነ ከባለስልጣኑ ውጭ ካሉ ሰዎች ወይም ሁለቱንም በማቀናጀት በአፈጣኝ ይመድባል፡፡	2) If the authority confirms that there is sufficient reason to conduct an investigation according to sub- article (1) of this article, it will promptly assign an investigator or more than one investigator from among the authority's employees or from people outside the authority, or a combination of both, depending on the severity of the case.
3) ማንኛውም ድርጅት ለሚደረገው ምርመራ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡	3) Any organization should provide all necessary cooperation for the investigation.
4) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ምርመራ እንደሚካሄድ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡ ሆኖም ይፋ ማድረጉ የምርመራውን ሂደት ያደናቅፈዋል ብሎ ካመነ ጉዳዩን በሚስጥር በመያዝ ድንገተኛ ምርመራ ማከናውን ይችላል፡፡	4) The authority must announce that an investigation will be conducted in accordance with sub article (1) of this article. However, the Authotity may conduct an emergency investigation keeping the matter confidential altogether upon ascertaining that disclosure would hamper the investigation process,
5) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ምርመራ በሚያከናውንበት ወቅት የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸሙ የሚጠቁም ማስረጃ ያገኘ እንደሆነ ወዲያውኑ እንደአግባብነቱ ሥልጣን ላለው ፖሊስ ወይም ዐቃቤ ሕግ ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡	5) If the authority finds evidence of a criminal act while conducting an investigation in accordance with this article, he must

	immediately notify the police or prosecutor as appropriate.
10. ምርመራን ለማድረግ የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች	**10. Sufficient grounds for investigation**
1) ማንኛውም ህግን የሚቃረን ድርጊት ስመፈጸሙ ማስረጃ መገኘቱ በአዋጁ አንቀጽ 77 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ምርመራ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት እንዳለ ይቆጠራል፡፡	1) The presence of evidence of any act against the law is considered to be sufficient reason to conduct an investigation according to Article 77 Sub-Article 2 of the proclamation.
2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትሁኔታች ምርማራ ለማካሄድ እንደ በቂ ምክንያት ይቆጠራሉ፡፡	2) Subject to the provisions of sub- article one of this article, the following circumstances shall be considered sufficient grounds for conducting an investigation.
ሀ. ህገ ወጥ የሆኑ ድርጊቶችን መፈጸም፤	a. commit illegal acts;
ለ. በባለስልጣኑ የማይታወቅ የባንክ አካውንት መክፈትና መጠቀም፤	b. Opening and using a bank account unknown to the authority;
ሐ. የድርጅት የሂሳብ እንቅስቃሴን በግለሰብ ስም ማካሄድ ወይም በጋራ መንቀሳቀስ የሚገባውን የባንክ ሂሳብ በአንድ ግለሰብ ስም ማንቀሳቀስ፤	c. Conducting corporate account activity in the name of an individual or operating a bank account that should be jointly operated in the name of an individual;
መ. የውጭ ዜጎችን አግባብ ያለው የስራ ፈቃድ ሳይዙ በድርጅቱ ማሰራት፤	d. Employing foreigners in the company without proper work permit;
ሠ. ከዕቃ ግዢ እና ንብረት አስተዳደር እና ንብረት ማስተላለፍ ጋር የተያያዙ ህገወጥ አሰራሮች መኖር፤	e. Existence of illegal practices related to procurement and asset management and asset transfer;
11. የምርመራ ስፋት እና የግዜ ሰሌዳ	**11. Scope and Time Table of Investigation**
1) የምርመራ ስራዎች በተቻለ ፍጥነትና በአጭር ግዜ እንዲሁም የድርጅቱን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴና ሕልውና አደጋ ላይ በማይጥል	1) Before entering into the investigation process, the authority should make appropriate

መልኩ እንዲጠናቀቁ ወደ ምርመራ ሂደት ከመግባቱ በፊት ባለስልጣኑ ተገቢውን ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡	preparations and precautions so that the investigation works can be completed as soon as possible and in a short time and in a manner that does not endanger the day-to-day activities and existence of the organization.
2) በተለየ ሁኔታ የምርመራው ስፋትና ጥልቀት ግምት ውስጥ በማስገባት በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በበቂ ምክንያት ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ምርመራ ቢበዛ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡	2) Any investigation shall be completed within a maximum of 30 working days, unless otherwise authorized by the Director General of the Authority, taking into account the scope and depth of the investigation.
3) ባለስልጣኑ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 በተጠቀሰው የግዜ ገደብ ውስጥ ምርመራውን የማያጠናቅቅ ከሆነ ምርመራውን ማቋረጥና ድርጅቱ ወደ መደበኛው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እንዲገባ ማድረግ ይኖርበታል፡፡	3) If the authority does not complete the investigation within the time limit mentioned in sub- article 2 above, he should terminate the investigation and allow the organization to return to normal daily activities.
4) ባለስልጣኑ የሚሰይመው መርማሪ የምርመራ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የድርጅቱን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴና ሕልውና አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ መሆን አለበት።	4) The investigator appointed by the authority must be in a manner that does not endanger the day-to-day activities and existence of the organization during the investigation.
12. የምርመራ ሥራ መከተል ስላለባቸው ሂደቶች	**12. Procedures to be followed for investigative work**
በባለስልጣኑ የሚመራ ማንኛውም አይነት ምርመራ የሚከተሉትን ሂደቶች መከተል ይኖርበታል፤	Any investigation conducted by the Authority shall follow the following procedures;
1) ምርመራውን ለመጀመር ምክንያት የሆነውን ጉዳይ መለየት፤	1) Identify the issue that led to the initiation of the investigation;
2) የምክንያቱን ትክክለኛነት ለመፈተሽና ይህንኑ ለማረጋገጥ ተጨማሪ ማስረጃ ማሰባሰብ እና በባለስልጣኑ ይዞታ ስር የሚገኙ የድርጅቱን ፋይሎች እና ተያያዥ ሰነዶች መመርመር ፤	2) To check the validity of the reason and to collect additional evidence to verify the same and examine the organization's files and related documents in the authority's possession;

3) የምርመራው ፍሬ ነገር በሁሉን አቀፍ ምርመራ ወይም በተለየ ጉዳይ ምርመራ አካሄድ መቀጠል እንዳለበት መወሰን፤	3) Determining whether the substance of the investigation should proceed through a comprehensive investigation or a case-by-case investigation;
4) ከዴስክ ምርመራው ውጤት በመነሳት ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልግ እንደሆነ ስመወሰን እና ፍቃድ ለማግኘት ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብና ማጸደቅ፤	4) Based on the results of the desk investigation, to decide whether further investigation is needed and to make a decision proposal to the director general of the authority and approve it;
5) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመስክ ምርመራ ማካሄድ፤	5) Conduct field investigation when necessary;
6) የሚመረመረው ድርጅት የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች በእያንዳንዱ የምርመራው ጭብጥ ዙሪያ የመሰማት መብታቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ፤	6) Ensuring that the managers and employees of the investigated organization have the right to be heard on each topic of the investigation;
7) የምርመራ ማጠቃለያ ሪፖርት ማዘጋጀትና የምርመራውን ውጤት ለባለስልጣኑ የበላይ አካል አቅርቦ ማጸደቅ፡፡	7) To prepare an investigation summary report and submit and approve the investigation results to the higher body of the authority.
13. በምርመራ ወቅት መወሰድ የሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች	**13. Precautions to be taken during examination**
ባለስልጣኑ በተለይም የመስክ ምርመራ በሚያከናውንበት ወቅት ሂደቱ የድርጅቶችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴና ሕልውና አደጋ ውስጥ እንዳይጥል የሚከተሉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ ይኖርበታል፤	The authority should take the following precautionary measures, especially during the field investigation, so that the process does not endanger the daily activities and existence of organizations;
1) በምርመራው መጀመር ሳቢያ በድርጅቱ ስጋቶች፣ ተጠቃሚዎች እንዲሁም በድርጅቱ ሰራተኞች ላይ የሚፈጠርን ግርታ ወይም ስጋት ለማስወገድ ምርመራውን ማወቅ ከሚገባቸው ሀላፊዎች እና የድርጅት ሰራተኞች በስተቀር በከፍተኛ ሚስጥር መያዝ እንዲሁም አስፈላጊውን ማብራሪያ ለተጠቀሱት አካላት መስጠት፤	1) In order to avoid any confusion or risk to the organization's donors, users and employees due to the start of the investigation, keep the investigation strictly confidential except for the officials and employees of the organization who should know about it, and give the necessary explanations to the mentioned parties;

2) በምርመራው ሂደት ላይ ንኡስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ምርመራውን በተመለከተ በባለስልጣኑ አመራሮች፤ የኮሚኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ እንዲሁም ባለስልጣኑ በሚወክለው ሰራተኞች አማካኝነት ብቻ መረጃ ለሚዲያና ለሚመለከተው አካላት ይፋ ማድረግ፤	2) In the course of the investigation, subject to sub- article 1, regarding the investigation by the authorities' leaders; Disclosure of information to the media and relevant parties only through the communication executive and the staff represented by the authority;
3) የድርጅቱ ተወካይ መገኘት የምርመራ ሂደቱን ያደናቅፈዋል በሚል አስቀድሞ ካልተወሰነ በስተቀር ምርመራው በድርጅቱ በአካል በመገኘት መከናወን በሚኖርበት ግዜ የድርጅቱ ሀላፊ ወይም ሃላፊው የወከለው ሰው፤ መርማሪዎች በቃል ለሚጠይቁት ማብራሪያ መልስ ለመስጠት አብሮ መገኘት ይኖርበታል ፤	3) The person in charge of the organization or the person represented by the person in charge of the organization when the investigation has to be conducted in person by the organization, unless it has been decided in advance that the presence of the representative will hinder the investigation process; He must be present to answer the verbal explanations asked by the investigators;
4) ባለስልጣኑ የምርመራ ስራውን በሚያካሂድበት ገዚ ያለባለስልጣኑ ፈቃድ በደርጅቱ ወይም በእርሱ ስም የተከፈተን የባንክ ሂሣብ እንዳይንቀሳቀስ ሲያግድ የድርጅቱ ተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ፤ የሰራተኞች ደሞዝ እንዳይቋረጥ እንዲሁም ለአስቸኳይ ስራ ገንዘብ ማንቀሳቀስ እንዲችል በልዩ ሁኔታ ሲፈቅድ ይችላል፤	4) When the authority, while conducting the investigation work, blocks the operation of the bank account opened by the organization or in his name without the permission of the official, so as not to harm the users of the organization; It may specifically authorize the freeze of workers' wages and the mobilization of funds for urgent work;
5) በማንኛውም ሁኔታ የመስክ ምርመራ የሚካሄደው በድርጅቱ የስራ ሰዓት መሆን ይኖርበታል፡፡	5) In any case, the field inspection should be conducted during the working hours of the organization.
14. መርማሪው ሊከተላቸው ሰለሚገባው ሥነ ምግባር	**14. Ethics that the investigator should follow**

ማንኛውም መርማሪ፤ 1) በዚህ መመሪያና አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች የተቀመጡትን የምርመራ አካሄድና ዘዴዎችን ተከትሎ መስራት ይኖርበታል፤	Any investigator; 1) He should work following the investigative procedures and methods set forth in this directive and other relevant laws;
2) ሙያውን የሚያከብር፣ ስራውን በአዋጁ፣በደንቡ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የሚያከናውን መሆን አለበት፤	2) He must respect his profession and perform his work in accordance with the proclamation, regulations and other relevant laws;
3) የጥቅም ግጭት ከተከሰተ ማሳወቅ አለበት እንዲሁም የሌሎች ያልተገባ ተጽዕኖ ሙያዊ ውሳኔዎችን እንዲያዛቡበት መፍቀድ አይኖርበትም፤	3) must disclose any conflict of interest and must not allow undue influence of others to distort his professional decisions;
4) በህግ የሚገደድ ወይም መረጃው ለማግኘት ስልጣን ላለው ሰው ካልሆነ በስተቀር በስራ አጋጣሚ የተገኙ መረጃዎችን አሳልፎ መስጠት አይኖርበትም፤	4) He must not hand over information obtained in the course of work except to a person who is required by law or has the authority to obtain the information;
5) በከፍተኛ ደረጃ ተአማኒነትን በተላበሰ መንገድ ሥራውን ማከናወን እና ታአማኒነቱን ጥያቄ ውስጥ ከሚጥሉ ከማናቸውም ተግባር መቆጠብ አለበት፤	5) He must perform his duties in a highly credible manner and refrain from any actions that call his credibility into question;
6) ምርመራውን ሲያከናውን ምርመራው የሚመለከታቸውን ሰዎች በአክብሮት ፣ በፍትሃዊነት ፣ ከስሜትና ከአድልዎ ነፃ በሆነ እና ስብዕናቸውን በማይነካ መንገድ ማካሄድ አለበት	6) When carrying out the investigation, the investigation must be conducted with respect, fairness, impartiality and impartiality of the persons concerned.
7) ምርመራዎችን ከግል ፍላጎት ነፃ በሆነ ሁኔታ በገለልተኛነት ማከናወን፣ እያንዳንዱን ጉዳይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች መመዘን እና የተለዩ ሃሣቦችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን አለበት፤	7) To carry out investigations independently of personal interest, to evaluate each case from different angles and to be ready to accommodate different opinions;

8) ምርመራን ስማከናወን የሚያስችለው በተለይም እውነቱን ለማውጣት የሚያስችል መሠረታዊ የሆኑ ክህሎቶች ያለውና ቢያንስ ለምርመራ መሠረት የሆኑትን ሕጎች ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆን አለበት፤	8) He must have the basic skills to carry out an investigation, especially to find out the truth, and at least he must be familiar with the laws that are the basis for an investigation;
9) የተመርማሪዎች የግል መረጃ የመጠበቅ መብትን ጨምሮ ሌሎች ሕጋዊ መብቶቻቸውን ማክበር አለበት፤	9) must respect other legal rights of investigators, including the right to privacy;
10) የምርመራ ውጤቶቹ ተጨባጭና በእውነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡	10) It should be ensured that the results of the investigation are objective and based on the truth.
15. ስለጥቆማ	**15. Report**
1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለባለስልጣኑ የሚቀርብ ጥቆማ ስም ተገልጾ ወይም ሳይገለጽ ባለስልጣኑ ባመቻቸውና ለሕዝብ ባሳወቀው፤ በጽሁፍ ወይም በሌላ አስተማማኝ መንገድ የመጠቆሚያ መንገድ ሊቀርብ ይችላል።	1) In accordance with sub-article (1) of Article 9 of this directive, a suggestion submitted to the authority, whether or not the name has been disclosed, has been arranged by the authority and notified to the public; A written or other reliable means of referral may be provided.
2) አንድን ጥቆማ ባለስልጣኑ ባመቻቸውና ለሕዝብ ባሳወቀው የመጠቆሚያ መንገድ ወይም በጽሁፍ ከደረሰ ባለስልጣኑ ጥቆማውን እንደደረሰው ይቆጠራል።	2) If a suggestion is received by the authority in the manner of suggestion arranged by the authority and notified to the public or in writing, the authority shall be deemed to have received the suggestion.

3) ባለስልጣኑ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን የሚቀበልበት የስራ ክፍል እና የሚመዘገብበት መዝገብ ያደራጃል፡፡ ምዝገባው ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፤	3) The authority will organize a work department to receive suggestions and a register to record them. The registration should include at least the following;
(ሀ) የሚታወቅ እና ፍቃደኛ ከሆነ የጠቋሚውን ስም፤	(a) the name of the informant, if known and willing;
(ለ) የጥቆማውን ፍሬ ሀሳብ ፤እና	(b) the substance of the suggestion; and
(ሐ) ጥቆማውን አስመልክቶ ስለተወሰደው እርምጃ፡፡	(c) About the action taken on the recommendation.
16. ከድርጅት ሰራተኞች ስሚቀርብ ጥቆማ	**16. Suggestions from company employees**
1) ባለስልጣኑ ከድርጅት ሰራተኞች የሚቀርቡ ጥቆማዎች በጠቋሚዎች የስራ ዋስትና ላይ አደጋ እንዳያስከትሉ ጉዳዩን በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝ ይኖርበታል፡፡	1) The authority should handle the matter with great care so that the suggestions from the employees of the organization do not endanger the job security of the indicators.
2) ባለስልጣኑ ድርጅቶች የሚሰጡት የቅጥር ውል ስምምነት ማቋረጥ ውሳኔ ለባለስልጣኑ ከቀረበ የምርመራ ጥቆማ ጋር የተገናኘ ነው የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የምርመራው ውጤት እስኪታወቅ ድረስ የቅጥር ውል ማቋረጥ ውሳኔው ውጤት እንዳይኖረው ለማድረግ ጥቆማው የቀረበው የቅጥር ውል ስምምነት ከተቋረጠ በኋላ አለመሆኑን በማረጋገጥ አግባብነት ካለው አካል ወይም ሀላፊ ጋር በትብብር ይሰራል፡፡	2) When the authority has sufficient suspicion that the decision to terminate the employment contract is related to an investigation suggestion submitted to the authority, it shall cooperate with the relevant body or official by ensuring that the suggestion is not made after the termination of the employment contract so that the decision to terminate the employment contract does not take effect until the results of the investigation are known:
17. በምርመራ ሂደት ባለስልጣኑ ስለሚኖረው ሥልጣን	**17. About the authority of the authority in the process of investigation**

1) ባለስልጣኑ የምርመራው ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከባድ የሕግ ጥሰት መፈጸሙን ሲያረጋግጥና በዚህም ምክንያት ድርጅቱ የተወሰነ ወይም አጠቃላይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ ማገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፣የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ምርመራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ፤	1) When the authority confirms that a serious violation of the law has been committed during the investigation, and as a result finds it necessary to suspend the organization from carrying out specific or general activities, the executive director of the authority until the investigation is completed;
(ሀ) ደርጅቱን የተወሰኑ እንቅስቃሴዎች እንዳያደርግ ማገድ፤	(a) prohibit the organization from carrying out certain activities;
(ለ) የድርጅቱ መታገድ በተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት የሚያደርስ የሆነ እንደሆነ ለተጠቃሚዎች የሚሰጡ አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች እንዳይቋረጡ የሚያደርጉ የተወሰኑ ሥራዎች ብቻ እንዲያከናውን ማድረግ፤	(b) if the suspension of the organization is harmful to the users, it will only perform certain tasks that will prevent the interruption of essential services provided to the users;
(ሐ) ከምርመራው ጋር ግንኙነት አለው ብሎ የሚጠረጥረውን ማናቸውም ግብይት ወይም ክፍያ ማስቆም ወይም ገንዘብ እንዳይከፋፈል መከልከል፤	(c) suspend any transaction payment or disbursement of funds suspected to be related to the investigation;
(መ) ያለባለስልጣኑ ፈቃድ በደርጅቱ ወይም በእርሱ ስም የተያዘ ንብረት እንዳይተላለፍ ወይም በድርጅቱ ስም የተሰበሰበ ገንዘብ ወይም የተከፈተን የባንክ ሂሣብ እንዳይንቀሳቀስ ማገድ፤	(d) prohibiting the transfer of property held by the organization or on its behalf or the movement of money collected or bank accounts opened in the name of the organization without the permission of the authority;
(ሠ) ከምርመራው ጋር በተያያዘ ቀጥታ ግንኙነት አለው ተብሎ የሚጠረጠረውን የሥራ አመራር ወይም ሌላ ሠራተኛን በድርጅቱ አሰራር መሰረት እንዲታገድ የማድረግና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በተነሳው አመራር ወይም ሠራተኛ ምትክ ድርጅቱ ሠራተኛ እንዲመድብ ማድረግ፤	(e) to suspend the management or other employees who are suspected to be directly related to the investigation in accordance with the organization's procedures and, if necessary, to have the organization assign an employee to replace the suspended management or employee;

(ረ) ድርጅቱን ከሦስት ወራት ለማይበልጥ ጊዜ ማናቸውንም እንቅስቃሴ እንዳያደርግ ማገድ፤ ይችላል፡፡	(f) can ban the organization from doing any activity for a period of not more than three months;
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚተላለፍ ትእዛዝ በጽሑፍ ሆኖ እንደአግባቡ በተለይ ሲታገድ የታሰበውን እንቅስቃሴ ወይም እንቅስቃሴዎች፣ ሲቀጥሉ የሚገባቸውን አስፈላጊ አገልግሎቶች፣ እንዳይፈጸም የሚፈለገውን ግብይት ወይም ክፍያ፣ እንዳይተላለፍ የሚፈለገውን ንብረት ዝርዝር፣ እንዳይንቀሳቀስ የሚታገደውን የገንዘብ መጠን ወይም የባንክ ሒሣብ ወይም እገዳ የሚቆይበትን ጊዜ በግልጽና በማያሻማ መንገድ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡	2) An order passed in accordance with sub-article (1) of this article shall be in writing and, as the case may be, clearly state the actions or activities to be banned, the necessary services to be continued, the transaction or payment to be prohibited, the list of assets to be prohibited, the amount of money or bank account to be prohibited, or the duration of the prohibition. It should be unambiguous.
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚጣል እገዳ የሚቆየው የእገዳው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፡፡	3) The ban imposed under sub-article (1) of this article shall be for a period of not more than three months from the date on which the ban decision becomes effective.
4) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተጣለውን እገዳ፤	4) the suspension imposed by the authority under sub-article (1) of this article;
(ሀ) በማናቸውም ጊዜ ገደብ የተጣለበት ሁኔታ መስተካከሉን ሲያረጋግጥ ሲሽረው፤	(a) at any time, upon proving that the condition under which the restriction has been imposed, has been rescinded;
(ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ረ) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ቦርዱ ወይም ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሁኔታዎች ከተስተካከሉ የእግድ ጊዜውን በማሳጠር ሲያሻሽለው ይችላል፡፡	(b) Subject to the time limit referred to in sub-article (1) (f) of this article and the decision of the Board or the court under sub-article (5) of this article, the period of suspension may be shortened if circumstances improve.

5). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዋና ዳይሬክተር በሰጠው ውሳኔ ላይ ድርጅቱ ቅሬታ ካለው በአዋጁ አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ (5) በተደነገገው መሠረት ቅሬታውን ውሳኔው በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡ በቦርዱ ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ድርጅቱ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ ይችላል።	5). In accordance with sub-article (1) of this article, if the organization has a complaint against the decision of the director-general, he can submit the complaint to the board within 30 days of receiving the decision as per the provisions of sub-article (5) of article 77 of the proclamation. If the organization is dissatisfied with the decision of the board, it can file an appeal to the Federal High Court within 30 days from the date of the decision.
18.ሰነድ፣ መረጃ ወይም ማብራሪያ ስለመጠየቅ እና የመተባበር ግዴታ	**18. Obligation to request and cooperate with documents, information, or clarifications**
1) በባለስልጣኑ የተመደበው መርማሪ የምርመራ ዓላማን ለማሳካት፤	1) To achieve the purpose of the investigation assigned by the authority;
(ሀ) ማንኛውም ሰነድ ዋናውን ወይም ቅጂውን፤	(a) the original or copy of any document;
(ለ) ማንኛውንም ሰነድ የተወሰነ ክፍል፤	(b) any part of any document;
(ሐ) ማንኛውንም መረጃ ወይም ማብራሪያ፤ እንዲሰጠው ምርመራ የሚደረግበትን ድርጅት ወይም ምርመራ ከሚደረግበት ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለውን ወይም ሌላ ማንኛውንም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡	(c) any information or clarification; He may request in writing from the organization under investigation or any other civil society organization related to the matter under investigation.
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚቀርበው የጽሑፍ ጥያቄ፤ (ሀ) የሚፈለገውን ሰነድ፣ የሰነዱን ዓይነት፣ ዋናውን ወይም ቅጂውን መሆኑን፣ ከሰነድ ውስጥ	2) A written request to be submitted under sub-article (1) of this article; (a) the document required, the type of document, whether it is the original or a copy,

የሚወሰደውን ክፍል፣ የሚፈለገውን መረጃ ወይም ማብራሪያ፤	the part to be taken from the document, the information or explanation required;
(ለ) መረጃው መቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ፤ ማካተት አለበት፡፡	(b) It should include the time limit within which the information must be provided;
3) ማንኛውም ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚቀርብ ጥያቄ የመተባበር ግዴታአለበት፡፡	3) Any organization is obliged to cooperate with a request made under sub-article (1) of this article.
4) አንድ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተጣለበትን ግዴታ ለማክበር የሚያወጣውን ምክንያታዊ ወጪ ባለስልጣኑ መሸፈን ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ድርጅቱ በምርመራ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ድርጅቱ የወጣውን ወጪ ለባለስልጣኑ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡	4) The Authority shall cover the reasonable expenses incurred by an organization in complying with its obligations under sub-article (1) of this Article. However, if the organization is found guilty in the investigation, the organization is obliged to return the expenses to the authority.
5) አንድ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በምርመራ ጥፋተኛ ሆኖ የወጣውን ወጪ ለባለስልጣኑ ሲመልስ፤ ከአስተዳደራዊና ፕሮግራም ወጪ ውስጥ ሳይካተት ወጪው ራሱን በቻለ የወጪ መዝገብ እንዲመዘገብ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡	5) When an organization is found guilty of an investigation in accordance with sub-article (4) of this article and returns the expenses incurred to the authority; Excluding administrative and program expenses, it is mandatory to record the expenses in an independent expense register.
19. የተሰጠን ሰነድ፣ መረጃ ወይም ማብራሪያ በሚስጥር ስለመጠበቅ	**19. Confidentiality of documents, information, or explanations given to us**
1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 መሠረት የሚሰጥ ሰነድ፣ መረጃ ወይም ማብራሪያ በሕግ የተጣለን ሚስጥርን የመጠበቅ ግዴታን የሚጥስ መሆን የለበትም፡፡	1) The document, information, or explanation provided in accordance with Article 18 of this directive shall not violate the duty of confidentiality imposed by law.

2) መርማሪው ወይም ባለስልጣኑ ስምርመራ ዓላማ ከድርጅቱ ከተረከበው ሰነድ ወይም ከተሰጠው መረጃ ወይም ማብራሪያ ውስጥ ስምርመራ ጥቅም ላይ የማይውሉትንም በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡	2) The investigator or the authority has the obligation to keep confidential the documents received from the organization or the information or explanations that are not used for the investigation.
3) መርማሪው ወይም ባለስልጣኑ ስምርመራ ዓላማ ከድርጅቱ የተረከበውን ኦሪጂናል ሰነዶች ምርመራውን ሲያጠናቅቅ ለድርጅቱ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡	3) The investigator or the authority is obliged to return the original documents received from the organization for the purpose of investigation to the organization upon completion of the investigation.
20. መረጃዎችን በአግባቡ ስለመያዝ	**20. About handling information properly**
ለተደረሰበት ውሳኔ በማስረጃነት ወይም በመረጃነት ያገለገሉ ማናቸውም ሰነዶች ወይም የሰነዶች ቅጂዎች ወይም በጽሑፍ የሰፈሩ ማብራሪያዎች በአግባቡ ተደራጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡	Any documents or copies of documents or written explanations used as evidence or information for the decision reached should be properly organized.
21. የምርመራ ሪፖርት ስለሚይዛቸው ጉዳዮች	**21. Regarding the issues covered by the investigation report**
የምርመራ ሪፖርት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤ 1) ስምርመራው መነሻ የሆነውን የመረጃ ምንጭ፤	An investigation report should include the following; 1) the source of information that is the basis for the investigation;
2) በቢሮ ደረጃ የመረጃውን ትክክለኛነት ስማጣራት የተወሰደው እርምጃ እና የተደረሰበትን መደምደሚያ፤ 3) የተጠቀመባቸውን የምርመራ ዘዴዎችና ቅደም ተከተላቸው፤ 4) በምርመራ ሂደት የተከናወኑ ሥራዎች እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች፤	2) The steps taken to verify the accuracy of the information at the office level and the conclusions reached; 3) The investigation methods used and their sequence; 4) Work performed during the investigation process and problems encountered and solutions taken;

5) ከምርመራው ጋር በተያያዘ ለድርጅቱ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት ላለው ድርጅት የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ ምላሾች፤ 6) የምርመራው ውጤትና የተደረሰበት መደምደሚያ፤	5) In relation to the investigation, the questions and answers given to the officers and employees of the organization as well as to the organization related to the organization; 6) The results of the investigation and the conclusions reached;
7) የድርጅቱን አቋም አጠቃላይ ግምገማ፤ እና 8) የመርማሪው ግኝትና የውሳኔ ሀሳብ፡፡	7) General assessment of the organization's position; And 8) Investigator's findings and recommendations.
22. በድርጅት ላይ ስለሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች	**22. About the administrative measures taken against the organization**
1) በተደረገው ምርምራ ድርጅቱ አዋጁን፣ አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ወይም ሌሎች ሕጎችን ጥሶ ከተገኘ ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 78 መሠረት፤	1) According to Article 78 of the proclamation, if the organization is found to have violated the proclamation, the rules and regulations issued on the basis of the proclamation, or other laws during the investigation;
(ሀ) የተፈጸመው ድርጊት ቀላል የሆነ እንደሆነ እንደአግባቡ የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ወይም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የታየውን ጉድለት እንዲያስተካክል ዋና ዳይሬክተሩ ለድርጅቱ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ (ለ) ድርጅቱ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ማስተካከያ የማያደርግ ከሆነ ወይም ድርጅቱ የፈጸመው ጥፋት ከባድ መሆኑን ባለስልጣኑ ካመነ ወይም ሌላ ጊዜ ጥሰት ፈጽሞ ከተገኘ ዋና ዳይሬክተሩ ለድርጅቱ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤	(a) If the action is minor, the Director-General will give a written warning to the organization to take appropriate corrective action or correct the defect within a certain period of time; (b) If the organization does not make corrections according to the warning given, or if the authority believes that the offense committed by the organization is serious, or if any other violation is found, the director-general will issue a strict warning to the organization;
(ሐ) በተሰጠው ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መሠረት ድርጅቱ አሰራሩን የማያስተካክል ከሆነ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ድርጅቱ እንዲታገድ ሊወስን ይችላል፤ (መ) የዋና ዳይሬክተሩ ውሳኔ በቦርዱ ካልተነሳ ወይም በፍርድ ቤት ካልታገደ በቀር፣ የዕገዳ ውሳኔው	(c) If the organization does not correct its operations according to the strict warning given, the executive director of the authority may decide to suspend the company;

በተሰጠ በሦስት ወራት ውስጥ ድርጅቱ ማስተካከያ ካላደረገ በቦርድ ውሳኔ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡	(d) Unless the Director General's decision is revoked by the board or suspended by the court, if the organization does not make adjustments within three months of the suspension decision, it will be dissolved by the board's decision.
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) መሠረት የሚወሰድ የማስተካከያ እርምጃ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ማድረግንም ይጨምራል፡፡ 3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 (ሀ) የሚሰጥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የተፈጸመውን የሕግ ጥሰት፣ ሊደረግ የሚገባውን ማስተካከያ እና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መስተካከል እንዳለበት በግልጽ ማሳየት አለበት። ለማስተካከያ የሚሰጠው ጊዜም የተፈጸመውን ጉድለት ወይም ጥፋት ክብደትና የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።	2) Corrective action taken in accordance with sub-article (1) (a) of this article includes amending the organization's bylaws. 3) A written warning given in sub-article (a) of this article must clearly indicate the violation of the law, the correction that must be made, and the time frame in which it must be corrected. The time given for correction should take into account the severity of the defect or fault and the complexity of the case.
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (መ) በቦርዱ የመፍረስ ውሳኔ የተሰጠበት ድርጅት አባላት፣ መሥራችች ወይም ኃላፊዎች ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታቸውን በአዋጁ አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ። 5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ በድርጅቱ ማኅደር ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡	4) The members, founders or officers of the organization whose dissolution decision was issued by the board in sub-article (d) of this article may submit their complaints to the Federal High Court in accordance with sub-article (5) of article 78 of the proclamation within 30 days of the decision. 5) A warning issued under sub article (1) of this article shall be filed in the company's archives.
23. የመሰማት መብት	**23. Right to be heard**
1) ባለስልጣኑ በማናቸውም ድርጅት ላይ ማናቸውንም ዓይነት እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ድርጅቱ መከራከሪያዎቹንና ማስረጃዎቹን እንዲያቀርብ እና	1) Before the authority takes any action against any organization, the organization will be given

በተወሰደው እርምጃ ላይ ቅሬታውን እንዲያሰማ ለድርጅቱ ዕድል ይሰጠዋል፡፡ 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚደረግ ጥሪ በጽሑፍ ሆኖ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀንና ሰዓት የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡	an opportunity to present its arguments and evidence and complain about the action taken. 2) A summons made in sub-article (1) of this article must be in writing and state the date and time the case will be heard.
24. ሪፖርትንና ውሳኔን ይፋ ስለማድረግ	**24. Disclosure of report and decision**
1) በአንድ ድርጅት ላይ የተከናወነ የምርመራ ሪፖርት እና ሪፖርቱን መሠረት አድርጎ የተሰጠው ውሳኔ ቅጂ ወይም ግብረ መልስ ምርመራ ስተካሄደበት ድርጅት እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡ 2) ምርመራው የተካሄደው ጥቆማን መሠረት በማድረግ ከሆነ ባለስልጣኑ ጠቋሚው የተወሰነውን ውሳኔ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡	1) An investigation report conducted on an organization and a copy or feedback of the decision based on the report will be sent to the organization where the investigation was conducted. 2) If the investigation is conducted on the basis of a tip, the authority will inform the tip of the decision.
25. የዕግድ ውሳኔ ለቦርድ ስለማሳወቅና ስለማራዘም	**25. Notification and extension of suspension decision to the board**
1) ባለስልጣኑ የእግድ ትእዛዝ ሲሰጥ ለቦርዱ በግልባጭ ያሳውቃል፡፡ 2) ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 77 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት የተሰጠ የ 3 ወራት የእግድ ትእዛዝ የተጀመረ የምርመራ ስራ ለማጠናቀቅ በቂ አለመሆኑን ካረጋገጠ አገዳው እንዲራዘም ለቦርዱ ሲያመለክት ይችላል፡፡	1) When the authority issues a suspension order, it notifies the board in reverse. 2) If the authority finds that a 3-month suspension order issued in accordance with Article 77 sub-article 4 of the proclamation is insufficient to complete the investigation, it may apply to the Board for an extension of the suspension.
3) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ለቦርዱ በጽሁፍ የሚገባው የእግድ ማራዘሚያ ጥያቄ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን ይኖርበታል፤	3) The written request for suspension extension referred to in sub-article 2 to the board should contain the following details;

ሀ. ስዕግዱ መነሻ የሆነውን የምርመራ ፍሬ ሀሳብ፤ ለ. በመጀመሪያ የተሰጠው ዕግድ ለምን ያህል ግዜ የተሰጠ መሆኑን፤ ሐ. በእግዱ ወቅት ባለስልጣኑ ያከናወናቸውን የምርመራ ሂደቶች፤	a. The conclusion of the investigation that led to the ban; b. the period of the suspension given in the first place c. Investigation procedures carried out by the authority during the suspension;
መ. ተጨማሪ እገድ ያስፈለገበት ምክንያትና ሊደረጉ የታሰቡ ተጨማሪ ምርመራዎች፤ ሠ. የእግዳው መራዘም ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚኖረው ፋይዳ ረ. እገዱ ባይራዘምና በምርመራው ሂደት ድርጅቱ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውን ቢያከናውን በምርመራው ሂደት ላይ ወይም በተጠቃሚዎች መብት ላይ ወይም በድርጅቱ ህልውና ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ፤ ሰ. በእግዱ ወቅት ድርጅቱ መውሰድ ያለበት የማስተካከያ እርምጃ ካለ ፡፡	d. Reasons for further suspension and proposed further investigations; e. The benefit of extending the suspension to make a fair decision f. If the ban is not extended and the organization carries out its daily activities during the investigation process, the damage that may be caused to the investigation process or to the rights of the users or to the existence of the organization; g. If there is any corrective action to be taken by the organization during the suspension period.
26. የእገድ ውሳኔ ቀሪ በሚሆንበት ግዜ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች	**26. Actions to be taken when suspension decision is pending**
1) በአዋጁ አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ቦርዱ በዋና ዳይሬክተሩ የተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ የሚሽር ውሳኔ በሚሰጥበት ግዜ ወይም ውሳኔ ሳይሰጥ 3 ወር በሚያልፍበት ግዜ በዋና ዳይሬክተሩ የተሰጠ የእገድ ውሳኔ ቀሪ ይሆናል፡፡ 2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የእገድ ትዕዛዝ ቀሪ በሚደረግበት ግዜ ባለስልጣኑ ከ 5 ተከታታይ ቀናት ባልበለጠ ግዜ ውስጥ የእገድ ውሳኔውን ማንሳትና	1) According to article 77 sub-article 4 of the proclamation, when the board makes a decision to revoke a suspension order issued by the director-general, or when 3 months pass without a decision being made, the suspension decision issued by the director-general will remain in effect. 2) When the suspension order is pending in accordance with sub-article 1 above, the authority should withdraw the suspension

ይህንኑም የእግድ ትዕዛዙን ሳሳወቃቸው አካላት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡	decision within 5 consecutive days and inform the parties to whom the suspension order was notified.
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ባለስልጣኑ እግዱን የማያነሳ ከሆነ ድርጅቱ ቀነ ገደቡ እንዳለቀ ለባለስልጣኑ ቦርድ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ መደበኛ ስብሰባ ግዜውን ሳይጠብቅ ለቅሬታው አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡	3) If the authority does not lift the ban according to sub-article 2 of this article, the organization can submit a complaint to the board of the authority after the deadline. The board should respond to the complaint immediately without waiting for the regular meeting.
27. በምርመራ ሂደት በሚተላለፍ የእግድ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ	**27. An appeal against a suspension decision passed during an investigation**
1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 መሰረት የእግድ ውሳኔ የደረሰው ማንኛውም ድርጅት ውሳኔው በጽሁፍ በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡	1) According to article 25 of this directive, any organization that has received a suspension decision can submit a complaint to the board within 30 days of receiving the decision in writing.
2) በዋና ዳይሬክተሩ በተላለፈው የእግድ ውሳኔ ላይ ለቦርዱ የሚቀርብ ቅሬታ በጽሁፍ ሆኖ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርበታል፤	2) A complaint submitted to the Board on the suspension decision passed by the Director General should contain the following details;
ሀ. የድርጅቱን ስም፣ አድራሻ እና የምዝገባ ሰርተፍኬት ቁጥር፤ ለ. በባለስልጣኑ የተላለፈው የእግድ ትዕዛዝ ይዘት እና ለድርጅቱ በጽሁፍ የደረሰበት ቀን፤ ሐ. ይግባኝ የሚባልበት ፍሬ ነገርና ድርጅቱ ቅሬታውን መሰረት የሚያደርግበት ማስረጃ ዝርዝር፤ መ. ድርጅቱ የሚጠይቀው ዳኝነት፡፡	a. the organization's name, address, and certificate of registration number; b. The content of the suspension order issued by the authority and the date it was received in writing by the organization; c. A list of the substance of the appeal and the evidence on which the organization bases its complaint; d. Jurisdiction required by the organization.

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Authority for Civil Society Organization

ክፍል አራት **ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**	**Section Four** **Miscellaneous provisions**
28.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ይህ መመሪያ በወጣበት ቀን በመካሄድ ላይ ያለ ቁጥጥር፣ክትትልና ምርመራ በተጀመረበት መንገድ ይቀጥላል፡፡	**28. Transitional provision** On-going monitoring, surveillance, and investigation will continue in the same manner as on the date of issuance of this directive.
29.መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ባለስልጣኑ ይህንን መመሪያ በማናቸውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡	**29. Regarding the amendment of the directive** The Authority may amend this directive at any time.
30.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመ በኋላ በሲፈዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለሥልጣኑ ድህረገጽ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡	**30. Duration of the directive** After being signed by the Director General of the Authority, this directive shall be registered with the Federal Ministry of Justice and shall be effective from the date of publication on the Authority's website.
ሳምሶን ቢራቱ መንደሊ **የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን** **ዋና ዳይሬክተር**	**Samson Biratu Mendeli** **Director General of** **The Authority for Civil society organization**